# ጥቅምት 8 ቀን 2010 ዓ.ም.

## ርዕስ ዜና

- የተቃውሞ ስልፎች ዛሬም ቀጥለው ዋሉ
- ከጅጅጋና ከሌሎች ከተሞች ተፈናቅለው በመጠለያ ያሉ ዜጎች የደረሰባቸውን ግፍ ተናገሩ
- ስኳር ከብዙ አካባቢዎች እየጠፋ ነው በአንዳንድ ቦታም ዋጋ ከእጥፍ በላይ ጨምሯል
- የአባይ ግድብ የሚያስከትለው ክስተት የሚያጠናው የቴኪኒክ ኮሚቴ ሪፖርት በመዘግየቱ ግብጽ ያሳሳባት መሆኑ ተነገረ
- የኬኒያ የምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ባለስልጣን ስልጣናቸውን ለቀው አሜሪካ ገቡ
- በሱማሊያ ከተከሰተው የፈንጅ አደጋ ጋር ተያያዞ ሁለት ሰዎች ታሰሩ፤ ባለስልጣኖች ሕዝቡ ደም እንዲለግስ ጠየቀ
- ቶጎ ውስጥ ከሃይማኖት መሪው መታሰር ጋር ተያዞ በተነሳ ግጭት ሁለት ወታደሮችና አንድ ሰላማዊ ሰዎች ተገደሉ ተባለ

## ዝርዝር ዜናዎች

- ባለፉት ቀናት በተለያዩ ከተሞች ሲካሄዱ የነበሩ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በዛሬውም ቀን ቀጥለው ውለዋል። በዛሬው ቀን የተቃውሞ ስልፎች ከተካሄዱባቸው ከተሞች መካከል መቱ፤ በደሌ፤ መካቱሪ፤ ጫንጮ፤ ጃርሶ፤ ገብረጉራቻ ይገኙባቸዋል። በትናንትናው ዕለት በፍቼ፤ ጎሃጽዮንና ሰላሌ በተደረጉ የተቃውሞ ስልፎች ምክንያት ደጀን ላይ መኪኖች ለመቆም የተገደዱ መሆናቸው ተነግሯል። በሁሉም ቦታዎች በተደረጉ የተቃውሞ ስልፎች የወያኔን አገዛዝ በጽኑ የሚያወግዙ መፈክሮች የተሰሙ ሲሆን በአንዳንዶቹ ላይ ፖሊሶችና የሌሎች ብሔረሰብ አባላት ተሳታፊ መሆናቸውን ከተገኘው መረጃ ማወቅ ተችሏል።

- ከጅጅጋ ከተማና ከሌሎች የሶማሊያ ክልል አካባቢዎች ተፈናቅለው በመጠለያ ካምፕ ውስጥ የሚገኙ ዜጎች በወያኔው ልዩ ፖሊስ የደረሰባቸውን በደልና እንዲሁም በየመጠለያ ጣቢያዎቹ የሚኖሩበትን የስቃይ ኑሮ ሁኔታ ለቢቢሲ የዜና ተቋም መናገራቸው ተገለጸ። የቢቢሲ የዜና ወኪል በዛሬው ዕለት እንደዘገበው በየስደተኛ ካምፑ ውስጥ በመዘዋወርና ስደተኞችን በማነጋገር መረጃ መሰብሰቡን ገልጾ ዜጎች በወያኔው ልዩ ፖሊስ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተደበደቡ መንገድ ላይ እንደተጣሉ፤ ሴቶች ከባሎቻቸው እንዲለዩ መደረጉና  በጫካ ውስጥ እንዲቆዩ በማድረግ ለተከታታይ ቀናት ሲደፈሩ

እንደቆዩ ፤ ህጻናት ከወላጆቻቸው እንደተለዩ እንደገለጹለት ዘግቧል። አሁን ባለው የመጠላያ ቦታ ምግብ ባይጠፋም የህጻናት ምግብ አነስተኛ መሆኑ፤ የመታጠቢያና የመጸዳጃ አገልግሎት አነስተኛ መሆኑን የገለጹ ከመሆናቸው በላይ በወታደሮችና በጸጥታ ኃይሎች በኩልም በየጊዜው ማስጠንቀቂያና ዛቻ የሚደርስባቸው መሆኑን ተናገረዋል።

በተያያዘ ዜና በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ በሚዘዋወሩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ችግር የተፈጠረ መሆኑ ታውቋል። ከሶማሌ አካባቢ ወደ መሀል አገር የሚመጡ እንደፍራፍሬ ዓይነት ሸቀጠቆችን የያዙ መኪናዎችን በየቦታው ማለፍ ተከልክለው የቆሙ መሆናቸው ሲገለጽ ከኦሮሞ አካባቢ ወደ ውጭ የሚሸጡ የጫት ምርቶችም በስማሌ ክልል ባለስልጣኖች በተደረገው እገዳ ምክንያት ሊሸጡ ያልቻሉ መሆናቸውና በዚህም አርሶ አደሮች እየተጎዱ መሆናቸው ታውቋል።

- ስኳር ከብዙ አካባቢዎች እየጠፋ መሆኑ ሲነገር የተወሰነ መጠን በሚገኝባቸው በአንዳንድ አካቢውዎችም ነጋዴዎች በከፍተኛ ዋጋ በራሸን እየሸጡ መሆኑን የሚደርሱ መረጃዎች ይገልጻሉ። በአዲስ አበባ ስኳር በአብዛኛቹ ቀበሌዎች የጠፋ ሲሆን በሚገኝባቸው ቦታዎች በኪሎ 22 ሲሸጥ የነበረው ወደ አርባ ብር ከፍ ማለቱ ታውቋል። ከስኳር ምርት ጋር በተያያዘ የወያኔ ባለስልጣኖች በዘረፋ ተግባር ላይ መቆየታቸው በተደጋጋሚ መዘገቡ የሚታወቅ ሲሆን ሌብነታቸውን ለመሸፈን የስካር ምርት ኃላፊዎች በአሁኑ ወቅት ለደረሰው የስኳር መጥፋት መጠገን ያልቻሉ ፋብሪካዎች ማምረት ስላልቻሉ ነው በማለት ምክንያት ለመስጠት ይሞክራሉ። ሜቴክ በሚባለው የወያኔ የብዝበዛ ተቋም እየሰራቸው ነው የሚባሉት የጣና በለስ 1 የጣና በለስ 2 እና የኦሞ ኩራዝ የስኳር ፋብሪካዎች ብዙ ቢሊዮን ብር ወጭ የወጣባቸው ቢሆንም እስካሁን ድረስ ስራቸው ሙሉ በሙሉ ያልጠናቀቀ ከመሆኑንም በላይ በቂ ምርት ለማምረት ያልቻሉ መሆናቸው ይነገራል። እንዲያውም ተመርቶ የነበረው የሸንኮራ አገዳ ምርት ፋብሪካው ባለመስራቱ መበላሸቱን የዜና ምንጮች አጋልጠዋል።

- የግብጽ የወያኔና የሱዳን የውሃ ሚኒስትሮች በአዲስ አበባ ላይ ውይይት በሚካሄዱበት ወቅት ግብጽ በባለሙያዎች የሚጠናው የመጨረሻው የቴክኒክ ጉዳይ ሪፖርት መዘግየት ያሳሳባት መሆኑን መግለጿ ሚድል ኢስት ሞኒተር የተባለው ጋዜጣ ዘግቧል። ቢ አር ቢ እና ኤል እና አርተሊያ (BRL and Artelia) የተባሉት የፈረንሳይ ኩባንያዎች ባለፈው ዓመት ጥር ወር የመጀመሪያ ዙር ዘገባቸውን

ማቅረባቸው የሚታወቅ ሲሆን ይህንን የመጀመሪያ ዙር ዘገባ ግብጽ ስትቀበል ሱዳንና የወያኔ አገዛዝ ሳይቀበሉ የቀሩ መሆናቸው ይታወቃል። ጥናቱ መሸፈን አለበት በሚባሉ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ባለመደረሱ ምክንያት በአስራ አንድ ወር ውስጥ ይቀርባል የተባለው የአጥኚው ቡድን ዘገባ ዘጠኝ ወር ያለፈ መሆኑ ተነግሯል። የዘገባው መዘግየትና የግድቡ ስራ አለመቋረጥ ግብጽን በጣም ያሳሰበ መሆኑ ታውቋል።

- የኬኒያ የምርጫ ቦርድ ኮሚሽን ከፍተኛ ባለስልጣን የሆኑት ሚስስ ሮዝሊን አኮምቤ በኬኒያ የምርጫው ኮሚሽን ውስጥ ከፍተኛ ውጥረት ላይ ስላለ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሊካሄድ አይችልም በማለት ኃላፊነታቸውን ለቀው ወደ አሜሪካ የሄዱ መሆናቸው ገልጿል። ሴትየዋ ኮሚሽን ከፍተኛ የፖለቲካ ተጽእኖ ስላለበት ስምምነት ላይ ሊደርስ ያልቻለ መሆኑን ገልጸው በተከታታይ በወሰዷቸው አቋም ምክንያት በህይወታቸው ላይ አደጋ ሊጣል ይችላል ከሚል ስጋት ወደ ኃላፊነታቸውን ለቀው ወደ አሜሪካ የመጡ መሆናችውን ገልጸዋል። ከጥቂት ጊዜ በፊት የምርጫ ቦርዱ የአይቲ ኃላፊ መገደላቸውን አስታውሰው በሳቸውም ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ ሊደገም ይችላል ከሚል ፍራቻ መውጣታቸውን አስምረውበታል። በኮሚሽን ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የፓርቲያቸውን መመሪያ ብቻ የሚያስተጋቡ በመሆናችው ስምምነት ላይ መድረስ አይችሉም ያሉት ሚስስ አኮምቤ ባለፈው ምርጫ የተደረገው ስህተት አሁንም ሊደገም ይችላል ብለዋል። የኮሚሽኑ አባላት እና ሰራተኞች ከፖሊቲካ ደጋፊዎችና ከተቃዋሚዎች ከፍተኛ ማስፍራራትና ዛቻ እንደሚደርሳቸው ገልጸዋል። የኬኒያ ምርጫ ኮሚሽን ሊቀ መንበር በሴትዮ ስልጣን መልቀቅ ያዘኑ መሆናቸው ገልጸው የኬኒያ ባለስልጣኖች በምርጫው ሂደት ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ ቢያስጠነቅቁም የሚቀጥለው ምርጫ ተአማኒነት ይኖረዋል የሚል ማስተማመኛ የማይሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

- በቅርቡ በሶማሊያ ከተማ ፈንድቶ ከፍተኛ ጉዳት ካስከተለው ፈንጅ ጋር በተያያዘ ሁለት ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸው ታውቋል። አንደኛው ከባለስልጣኖች ጋር የሚተዋወቅ ከፍተኛ ቦታ ያለው ሰው ፈንጅው የጠመደበት ከባድ መኪና ወደ መሀል ሞቃዲሾ እንዲያልፍ ወታደራዊ ኃላፊዎችን አግባብቶ እንዲያምኑ አድርጓልል በሚል ምክንያት የታሰረ ሲሆን ሌላው ደግሞ በዚያኑ ዕለት ፈንጅ በተጠመደበት ፒክ አፕ መኪና ሆኖ ከባዱን የጭነት መኪና ሲከተል የነበረና በኋላም አቅጣጫ በመቀየር ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ የተያዘ አሽከርካሪ ነው። ሁለቱም ሰዎች ምርመራ እየተካሄደባቸው መሆኑ ታውቋል። በተያያዘ ዜና የሶማሊያ ባለስልጣኖች ቆስለው በህክምና ላይ ለሚገኙት ዜጎች ሕዝቡ ደም እንዲለግስ ተማጽነዋል። በርካታ ሰዎች በከባድ ሁኔታ ስለቆሰሉ የማቹ ቁጥር ሊጨምር ይችላል የሚለው ስጋት አሁንም ከፍተኛ ነው።

- ሰኞ ዕለት ቶጎ ውስጥ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙነት አላቸው የሚባሉ የሃይማኖት መሪ በመታሰራቸው ምክንያት ከፍተኛ ተቃውሞ ተነስቶ በተፈጠረ ግጭት ጉዳት የደረሰ መሆኑ ይታወቃል። ማክሰኞ ዕለት የቶጎ ባለስልጣኖች በሰጡት መግለጫ ሶስት ሰዎች የተገደሉ መሆናቸውንና ከእነዚህም ውስጥ ሁለቱ ወታደሮች እንደሚገኙበት ገልጸዋል። በመካከለኛው የቶጎ ግዛት በሚገኙ ሶኮዴ እና ባፊሎ በሚባሉ ከተሞች ተቃዋሚዎች ጎማ በማቃጠል መንገድ የዘጉ መሆናቸውና እንዲሁም በሎሜ ከተማ የሚገኘውን የተቃዋሚ ፓርቲ ጽ/ቤት ፖሊስ ያቃጠለው መሆኑን ተነግሯል።
-

# ጥቅምት 7 ቀን 2010 ዓ.ም.

## ርዕሰ ዜና

- የተቃውሞ ስልፎች ቀጥለዋል
- ፍሬደም ሀውስ የአሜሪካ ምክር ቤት አባላት ረቂቅ ህጉን ለማጽደቅ ጥረት ማደረግ አለባቸው አለ
- የወያኔው የኢንተርኔት አገልግሎት ከጎረቤት አገሮች ጋር ሲወዳደር በዋጋም ሆነ በጥራት ዝቅተኛ ነው ተባለ
- የተመድ ዋና ጸሐፊ በሳህል አካባቢ ያለው የሰላም አስከባሪ ኃይል እንዲጠናከር ጠየቁ
- በቱኒዚያ ባህረ ሰላጤ ስደተኞችን ጭኖ የነበረ የእንጨት ጀልባ በግጭት ሰጥሞ ጉዳት ደረሰ

## ዝርዝር ዜናዎች

- ሰኞ ጥቅምት 6 ቀን 2010 ዓ.ም. በተለያዩ ከተሞች የተቃውሞ ስልፎች ተደርገዋል። ስልፎቹ ከተደረጉባቸው ከተሞች መካከል በደሴ ሻምቡ ደንጎሮ መቱ ግምቢ ፍቼ እና አዳማ ይገኙበታል። ሰሞኑን በተለያዩ ከተሞች ሲካሄዱ የነበሩት ሰልፎች በማን እንደተደራጁ ግልጽ ባይሆንም ሲያቀነቅኗቸው የነበሩት መፈክሮች በአብዛኛው የወያኔ አገዛዝ የሚያወግዙ፤ መብትና ነጻነት

እንዲከበር እንዲሁም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ የሚጠይቁ ናቸው። አንዳንድ የሕዝብ ጠበቃ ነን የሚሉ ወገኖች በማን እንደተጠራ ግልጽ አይደለም በሚል ምክንያት ሰልፉን ለማዳነቀፍ እያደረጉት ያሉት ሙከራዎች ብዙዎችን አስገርሟል ተብሏል።

- ፍሪደም ሃውስ የተባለው ተቋም ሰኞ ጥቅምት 6 ቀን 2010 ዓም ባሰፈረው ዘገባ የአሜሪካን ምክር ቤት አባላት በወያኔ የይመስል ማስፈራርያ ሳይታላሉ ረጅም ጊዜ ያሰናዱትን የውሳኔ ረቅቂ ለማሳለፍ ጥረት ማድረግ አለባቸው ብሏል። በአገሪቱ ውስጥ የዜጎች የሰብአዊ መብት እንዲከበርና ሁሉም በእኩልነት የሚሰታፍበት የፖለቲካ ስርዓት እውን እንዲሆን የሚጠይቀው ኤች አር 128 በሚል ስም የሚታወቀው ረቂቅ ውሳኔ ከሁለቱም ምክር ቤቶች ቢያንስ የ 71 ዱ ድጋፍ የነበረው ሲሆን ለማለፍ ከፍተኛ እድል ነበረው። ይሁን እንጅ ውሳኔው የሚያልፍ ከሆነ የወያኔ አገዛዝ በምስራቅ አፍሪካና በሌሎች ቦታዎች በሚደረጉ የጸረሽብር ተግባር ላይ ተባባሪ አልሆንም የሚል ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ በመስጠቱ ውሳኔው ለላልተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ ተደርጓል ተብሏል። የወያኔ አገዛዝ ካለፈው ዓመት ጥር ወር ጀምሮ በአሜሪካ አገር የሎቢ ተቋም በመቅጠር የምክር ቤቱን አባላት አቋም ለማስቀየር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የቆየ መሆኑና በሎቢ ጥረት ብቻ ረቂቅ ውሳኔው እንዳያልፍ አደርጌያለውሁ ብሎ ሲፎክር መቆየቱ የሚታወቅ ነው። ይሁን እንጅ የሎቢውን ተጽዕኖ ተቋቋሞ እንደገና ያንሰራራው ረቂቅ ውሳኔ የብዙዎቹን የምክር ቤት አባላት ድምጽ በማግኘት ማለፉ ያሰደነገጠው ወያኔ የመጨረሻ ካርዱን በመምዘዝ በጸረ ሽብር ተግባር አልተባበረርም የሚል መልክት አስተላልፏል። የወያኔ አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ጭፍጨፋና አፈና ሲካሄድ ዓይን ዘግቶ ማሳለፍ ከአሜሪካ መንግስት በኩል የሚጠበቅ እርምጃ ባለመሆኑ ይህን ውሳኔ ለማሳለፍ የምክር አባላቱ ጠበቅ ያለ እርምጃ መወሰድ ይኖርባቸዋል በማለት ተቋሙ አሳስቧል።

- በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ከአንዳንድ የአካባቢ አገሮች ጋር ሲወዳደር ዋጋው ዝቅተኛ እና አስተማማኝ አለመሆኑን አንድ የቢቢሲ ዘገባ አጋለጠ። በኢትዮ ቴሌኮም የሚሰጠውን የኢንተርኔት አገልግሎት በተለይ ከኬኒያ ከታንዛኒያ እና ከግብጽ ጋር ያወዳደረው ይህ ዘገባ በአገራችን የሚሰጠው የኢንተርኔት አገልግሎት በዋጋ ደረጃ ከፍ ያለ፤ ወጥነት የሌለው ማለትም በአንድ ወቅት ዘለግ የሚል በሌላ ወቅት በአጭሩ የሚያልቅ በሞኖፖል የሚሰራ እና ተወዳዳሪዎች የሌሎት መሆኑን ገልጿል። ከኢትዮጵያ ጋር ሲወዳደር በኬኒያና በታንዛኒያ ፈጣን የሆነ አገልግሎት በርካሽ ዋጋ የሚገኝ መሆኑን ዘገባው በዝርዝር አስቀምጧል። የዋጋው ነገር እንዳለ ሆኖ በሌሎች አገሮች የሚገዙት የኢንተርኔት አገልግሎት አንድ ወጥ መሆናቸው ሲረጋገጥ በኢትዮጵያ ግን አንዳንድ ጊዜ ዘለግ በአንዳንድ ወቅት ደግሞ ለአጭር ጊዜ መሆኑን ዘገባው ጠቅሟል። ለምሳሌ በአምስት ብር

የኢትንተርኔት አገልግሎት አንዳንድ ጊዜ ረዥም ደቂቃዎች ሲኖሩት አንዳንድ ጊዜ በአጭር ጊዜ የሚያልቅ መሆኑን አውስቷል። በብዙ አገሮች የኢንተርኔት አገልግሎትን የሚሰጡ በርካታ ተቋሞች መኖራቸውና በመካከላቸው ውድድር መኖሩ በዝቅተኛ ዋጋ ጥራት ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት ሲቻል በኢትዮጵያ ግን ኢትዮቴሌኮም በሞኖፖል ይዞት ቆይቷል ብሏል።

- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒያ ጉተረትስ በሳህል አካባቢ የአክራሪዎችን ጥቃት ለመቋቋም የተሰማራውን 5000 አባላት የሚገኙበትን የሰላም አስከባሪ ጦር ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል። በአካባቢው ያለውን ሁኔታው በግንዛቤ ወስዶ አስችኳይ እርምጃ ካልተወሰደ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደታች እየወረደ የመጣው የሳህል የጸጥታ ሁኔታ ይብልጥ ሊበላሽ ይችላል በማለት ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል። ጦሩን ለማጠናከር የመሰረቱት አምስት አገሮች ማለትም ማሊ ሞሪታኒያ ናይጀር ቡርኪና ፋሶ እና ቻድ ኃላፊነት ቢኖራቸውም ከተመድ አባል አገሮች ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልግ መሆኑን ጠቁመዋል።

- እሁድ ጥቅምት 5 ቀን በቱኒዚያ ባህረ ሰላጤ አካባቢ አንድ የቱኒዚያ ባህር ኃይል መርከብ ስደተኞን ጭኖ ወደ አውሮፓ ከሚያመራ የእንጨት ጀልባ ጋር በመጋጨቱ 25 ስደተኞች የሞቱ መሆናቸው የቱኒዚያ ባለስልጣኖች ገልጸዋል። ጀልባዋ ላይ ከነበሩ መካከል 38 ሰዎች ህይወት የተረፈ ሲሆን ቁጥራቸው ያልታወቀ ስዎች እስካሁን መዳረሻቸው ያልታወቀ መሆኑ ታወቋል። ግጭቱ በምን ምክንያት እንደተፈጠረ ጥናት እየተደረገ ይገኛል። ከቱኒዚያ ወደ ጣሊያን የሚጓዙ ስደተኞች ቁጥር እየጨመረ ሲሆን ባለፈው ወር ብቻ ከ 1400 በላይ የሆኑ ቱኒዚያውያን ጣሊያን መግባታቸው ይታወቃል።፡

# ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም.

## <u>ርዕሰ ዜና</u>

- በርከት ስምኦን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰብሳቢነቱ ተነሳ የኃይለ ማርያም አማካሪ በመሆን ከነበረው ከፖሊሲ ጥናትና ምርመራ ኃላፊነቱም በጥያቄ ለቀቀ
- በተለያዩ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፎች ተደረጉ
- በዛምቢያ 70 ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ታሰሩ
- የግብጽ የመስኖ ሚኒስትር ወደ ኢትዮጵያ አመሩ
- በናይሮቢ ከተማ የተቃዋሚ ደጋፊዎች ለማኬሄድ የሞከሩትን ሰልፎች ፖሊስ የበተናቸው መሆኑ ታወቀ
- በግብጽ ሰሚናዊ ሲና ግዛት የአይሲስ ኃይሎች የግብጽ ወታደሮችን ገደሉ፤ አቆሰሉ

## ዝርዝር ዜናዎች

- ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ የወያኔው ባለስልጣን በረከት ስምኦን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቦርድ ሰብሳቢነቱ የተነሳ መሆኑን ከወያኔ አገዛዝ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳለው የሚታወቀው የሪፖርተር ጋዜጣ መዘገቡ የሚታወቅ ሲሆን ሰኞ ዕለት አንድ አፍቃሪ ወያኔ የሆነ ጦማሪ ደግሞ ግለሰቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ከነበረው ከፖሊሲ ጥናትና ምርመራ ኃላፊነት ለመሰናበት የስንብት ደብዳቤ አስገብቶ የተፈቀደለት መሆኑን ገልጿል። ባለፈው ሳምንት ውስጥ በረከት ስምኦን ወደ አሜሪካ ከእነቤተሰቡ መጥቶ በአሁኑ ወቅት በቨርጂኒያ ግዛት እንደሚገኝም ውስጥ አወቅ ምንጮች ገልጸዋል። የመለስ የቅርብ አሽከርና አገልጋይ የነበረው በርከት ባለፉት 25 ዓመታት በተለያዩ ቦታዎች ሀብት ማካበቱ የሚታወቅ ሲሆን በተለይ በባህርዳርና በጎንደር ከተሞች በሚስቱ ስም ሳይቀር የተለያዩ ከፍተኛ ሆቴሎች ባለቤት እንደሆነ ይነገራል። የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ ሲመጣ ከኃላፊነት በመባረርም ሆነ መሰናበት እንዲሁም አገር ጥሎ መሸሽ የተለመደ አካሄድ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ስልጣን ከመልቀቁ ጋር ተያይዞ የበረከት ከእነቤተሰቡ አሜሪካ መግባቱ የሽሽት እርምጃ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት የሚሰጡ በርካታ ናቸው።

- በትናትናው ዕለት በተለያዩ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፎች ሲካሄዱ የነበሩ መሆናቸው ተነግሯል። ከአዲስ አበባ ብዙም ርቀት በሌላት የሱሉልታ ከተማ ሕዝቡ በከፍተኛ ቁጥር በመውጣት ወያኔ የሚያወግዙ መፈክሮች ሲያሰማ የዋለ ሲሆን በዱከም ከተማ በተደረገ ሰላማዊ ስልፍ ደግሞ ሕዝቡ ይዞ ሲያስተጋባቸው ከነበሩት መፈክሮች መካከል ስኳር “ወደ ቀበሌ አባይ ጸሐዩ ወደ ከርቸሌ” የሚለው መፈክር እንድነበር የደረሱ መረጃዎች ይገልጻሉ።

- በዛሬው ቀን የዶክተር መራራ የክስ ጉዳይን ፍርድ ቤት ያየው ሲሆን ከዚህ በፊት የምስክሮች ስም ዝርዝር በይፋ በክሱ ሰነድ ላይ አለመገለጹ የተከሳሹን ህገ መንግስታዊ መብትን መገደብ ነው

ለሚለው ጥያቄ የፌዴሬሽን ጉዳይ ምክር ቤት በሰጠው መልስ የህገ መንግስት ክፍተት የለውም በሚል የመለሰ መሆኑ ታውቋል። በዚህ መሰረት አቃቤ ህግ የሚያቀርባቸው የሕግ ምስክሮች ማንነታቸው ይፋ ሳይወጣ እንዲመሰክሩ ፍርድ ቤቱ ለጥቅምት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. የተቀጠረ መሆኑ ታውቋል።

- ቅዳሜ ጥቅምት 4 ቀን ለእሁድ አጥቢያ በሉሳካ ዛምቢያ ፖሊሶች በፍተሻ 70 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን የያዙ መሆናቸውን የዛምቢያ ባለስልጣኖች ተናግረዋል። ስደተኞቹ የተያዙት በአንድ ትምህርት ቤት አጠገብ በምትገኝ አነስተኛ ጎጆ ውስጥ ሲሆን ፖሊስ መረጃዎን ያገኘው ከአካባቢው ነዋሪዎች መሆኑን ተገልጿል። ስደተኞቹን ያመጧቸው ግለሰቦች እየተፈለጉ መሆናቸውን ባለስልጣኖች ገልጸው ከተያዙ ከ15 እስከ 20 ዓመት እስራት እንደሚበየንባቸው ተናግረዋል። የስደተኞች ዕጣ ፋንታ ለጊዜው ምን እንደሆነ ባይታወቅም ለወያኔ አገዛዝ ይሰጣሉ የሚል ስጋት አለ።

- የግብጽ የመስኖ ሚኒስትር እሁድ ጥቅምት 5 ቀን 2010 ዓም. ወደ አዲስ አበባ የሄዱ መሆናቸውን አህራም ኦን ላይን የተባለው የግብጽ ድረ ገጽ ጋዜጣ ገልጿል። ሚኒስትሩ ወደ አዲስ አበባ የሄዱት በአባይ ግድብ ቴክኒካል ጉዳይ ለመወያየት ሶስቱ አገሮች በሚያካሄዱት የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ለመገኘት ከመሆኑም በላይ የአባይን ግድብ በአካል በመጎብኘት ስለቴክኒያዊ ጉድለቱ ግንዛቤ ለማግኘት ነው ተብሏል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግብጽ ግድቡ ስለሚያስከትለው ጉዳት ቅሬታዋን ስታሰማ መቆየታ የሚታወቅ ሲሆን በአሁኑም ስብሰባ ላይ ይህንን አቋሟን ስታጸባርቃለች የሚል ግምት ተወስዷል። ባለፈው መስከረም ወር ከሶስቱም አገሮች የተውጣጣው የቴክኒክ ኮሚተ ካርቱም ላይ መሰብሰቡ ሲታወቅ ቢአር ኤል እና አርተሊያ (BRL and ARTELIA) የተባሉት የፈረንሳይ የቴክኒክ ባለሙያዎች ቡድኖች የሰጡትን የመጀመሪያ ዙር ሪፖርት አዳምጠዋል። የቡድኑ የመጨረሻ ዙር ሪፖርት በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ሊጠናቀቅ ይችላል ተብሎ ተገምቷል።

- በሶማሊያ ባለፈው ቅዳሜ በተከሰተው ፈንጂ ሳቢያ የሞቱት ሰዎች ቁጥር 300 የደረሰ መሆኑንና ከ400 በላይ የሆኑ ሰዎች የአካል ጉዳተኞች መሆናቸው ለማወቅ ተችሏል። አንድ የቱርክ ወታደራዊ አውሮፕላን መድሃኒቶችንና የህክምና መሳሪያኦችን ይዞ ወደ ቦታው የመጣ ሲሆን ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ ጉድት የደረሰባቸውን አርባ የሚሆኑ ቁስለኞች ወደ አገራቸው ወስደው ለማከም

መስማማታቸውን የቱርክ ባለስልጣኖች ገልጸዋል የአካባቢው አገሮችም ዶክተሮችና የህክምና መሳሪዎች እየላኩ መሆናቸው ተነግሯል። እሁድ ዕለት የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የሞቃዲሹ ነዋሪዎች በድርጊቱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ሲያሰሙ የዋሉ ሲሆን አልሸባብንም ሲያወግዙ ተስተውሏል። አለሸባብ እስካሁን ድረስ ለድርጊቱ ኃላፊነቱ መውሰዱን የሚያረጋግጥ መግለጫ አለማውጣቱ ይታወቃል።

- ዛሬ በናይሮቢ የተቃዋሚው መሪ የራይላ ኦዲንጋ ደጋፊዎች ስልፍ ለማደረግ ያደረጉት ሙከራ በፖሊሶች የተበተነ ሲሆን ፖሊሶች አንድ የመንገድ ላይ ነጋዴም ተኩሰው የገደሉ መሆናቸው ታውቋል። ባለፈው ሳምንት የኬኒያ መንግስት በሶስት ከተሞች ላይ ተቃውሞ ስልፍ እንዳይደርግ ቢከለክልም ስልፎቹ ምንም ሳያግዳቸው ሲደረጉ ቆይተዋል። ሚስተር ኬኒያታ ማሸነፋቸው ከተገለጸበት ካለፈው ዓመት ነሐሴ ወር ጀምሮ በፖሊስ የተገደሉት ሰዎች ቁጥር 67 መድረሱን አምነስቲ ኢንተርናሽናል ሂውማን ራይትስ ዎች የተባሉት የሰብአዊ መብት ተከራራክሪ ድርጅቶች በቅርቡ በጋራ ባወጡት ዘገባ ገልጸዋል። 151 የሚሆኑ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን፤ ምስክሮችንና ፖሊሶችን እንዲሁም ሌሎች ሰዎችን በማነጋገር የተጠናከረው ዘገባ ፖሊሶች በተለያዩ ከተሞች ኦፕሬሽን በማካሄድ የቤት በር እየሰበሩ ነዋሪዎችን መግደላቸውንና አስረው ማሰቃየታቸውን እንዲሁም ማስፈራራታቸውን አጋልጧል። ዘገባው ይህ አሰራር ባስቸኳይ መቆም እንዳለበት ገልጾ ከሚቀጥለው ምርጫ በፊት ሰላማዊ ሁኔታ መፈጠር አለበት ብለዋል። የኬኒያ መንግስት ዘገባውን መሰረተ ቢስ ነው በማለት አጣጥሎታል።

- እሁድ ጥቅምት 5 ቀን 2010 ዓ.ም በግብጽ በሰሜናዊ ሲናይ ግዛት የአይሲስ ኃይሎች በስድስት የመፈተሻ ጣቢያዎች ላይ ጥቃት በማደረስ 7 ወታደሮችን የገድሉ መሆናቸውና ሌሎች 37 የሚሆኑትን ያቆሰሉ መሆናቸውን የግብጽ ባለስልጣኖች እና የሆስፒታል ኃላፊዎች ገልጸዋል። አጥቂዎቹ አውቶማቲካ መሳሪያ በመተኮስ ሼክ ዘውዲ በተባለችው ከተማ ውስጥ የሚገኙትን መፈተሻ ጣቢያዎች ያጠቁ ሲሆን ጥቃታቸው ተገድቦ ወደ ኋላ ሊመለሱ የቻሉት በሄሊኮፕተር አማካይነት ጦርነት ከተደረገ በኋላ ነው ተብሏል። 24 አሸባሪዎች እንደሞቱና ሁለት የመጓጓዣ መኪናዎች እንደተቃጠሉባቸው የግብጽ ወታደራዊ ቃል አቀባይ ገልጿል።